የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 36
ADDIS ABABA 11th May 2017

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፬፻፫/፪ሺ፱ ዓ.ም**

ብሄራዊ የስነ-ልክ አገልግሎቶች ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..................ገጽ ፱ሺ፮፻፴፩

ማረሚያ ቁጥር ፱/፪ሺ፱ እና ቁጥር፲/፪ሺ፱......ገጽ ፱ሺ፮፻፴፫

**CONTENT**

Regulation No. 403/2017

Rate of Fees for National Metrology Services Council of Ministers Regulation ………………………………page 9631

Corrigendum No.9/2017 and No. 10/2017………page 9633

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፫/፪ሺ፱

## ብሔራዊ የስነ-ልክ አገልግሎቶች ክፍያ ተመን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፱ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯ (፩) እና ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፬/፪ሺ፪ አንቀጽ ፮(፲፰) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "ብሄራዊ የስነ-ልክ አገልግሎቶች ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፫/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 403/2017**

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE FEE PAYABLE FOR NATIONAL METROLOGY SERVICES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015, Article 17(1) the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and Article 6(18) of the National Metrology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 194/2010.

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the “Rate of Fees for National Metrology Services Council of Ministers Regulation No. 403/2017.”

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ደንብ" ማለት ብሄራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፬/፪ሺ፫ ነው፡፡

፪. "አክሪዲቴሽን" ማለት የካሊብሬሽን ላብራቶሪ፣ ፍተሻ ላብራቶሪ፣ ሰርተፊኬሽን እና ኢንስፔክሽን ተግባር የሚያከናውን ድርጅት ብቃት ያለው መሆኑን በሚመለከት የሚሰጥ ምስክርነት ነው፡፡

፫. በደንቡ የተጠቀሱት ትርጓሜዎች ለዚህም ደንብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ፫. ስለ አገልግሎት ክፍያ

ለመለኪያ መሳሪያዎች ካሊብሬሽን እና ለስነ-ልክ አገልግሎቶች፣ ለስነ-ልክ ዘርፍ ስልጠናና ምክር አገልግሎቶች፣ ለሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና፣ ተከላና ኮሚሽኒንግ አገልግሎቶች፣ ለሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ስልጠናና ምክር አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ለስነ-ልክና ሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎቶች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል።

## ፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1. "Regulation" means National Metrology Institute Establishment Council of Ministers Regulation No 194/2010.
2. "Accreditation" means attestation related to a Calibration, Inspection, Certification body conveying formal demonstration of its competence to carry out specific Calibration, Inspection and Certification tasks.
3. Definitions provided under the Regulation shall be applicable for this Regulation.

## 3. Service Fees

Service fees shall be payable for services rendered for Measuring instrument calibration and Metrology services, Metrology training and Consultancy services, Scientific equipment installation commissioning and maintenance services, Scientific equipment training and consultancy services, Metrology and Scientific equipment competency assurance services in accordance with table attached herewith.

## 4. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of May, 2017.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ማረሚያ ቁጥር ፱/፪ሺ፱

ለአዲስ አበባ የኃይል ማስተላለፊያ መረብ ማሻሻያ እና ደረጃውን ማሳደጊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢንፖርት ባንክ የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፯/፪ሺ፱ በመግቢያውና በአንቀጽ ፫ "በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩ ቢሊዮን ፻፵፭ ሚሊዮን( አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ አርባ አምስት ሚሊዮን የቻይና ዩዋን)" የተባለው "በብድር ስምምነቱ የተገኘው ፩ ቢሊዮን ፬፻፵፭ ሚሊዮን( አንድ ቢሊዮን አራት መቶ አርባ አምስት ሚሊዮን የቻይና ዩዋን)" ተብሎ ይነበብ። በተጨማሪም በእንግሊዝኛው "Done at Addis Ababa this 27th day of January 2016" የተባለው "Done at Addis Ababa 27th day of January 2017" ተብሎ ይነበብ።

## ማረሚያ ቁጥር ፲/፪ሺ፱

ለብሔራዊ የኃይል አቅርቦት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፩ /፪ሺ፱ "Done at Addis Ababa this 27th day of January 2016" የተባለው "Done at Addis Ababa 27th day of January 2017" ተብሎ ይነበብ።

## Corrigendum No.9/2017

On Preamble and Article 3 Export-Import Bank of China Loan Agreement for financing the Addis Ababa Power Network Rehabilitation and Upgrading Project Ratification Proclamation No.987/2016 "a Loan in an amount equivalent to 1,145,000,000 yuan (one billion one hundred forty five million Chinese yuan) is hereby corrected and shall be read as "a Loan in an amount equivalent to 1,445,000,000 yuan (one billion Four hundred forty five million Chinese yuan). In addition "Done at Addis Ababa this 27th 2016 "is hereby corrected and shall be read as "Done at Addis Ababa this 27th day of January 2017.

## Corrigendum No. 10/2017

Agence Franciase De Development (AFD) Credit Facility Agreement for financing of the National Load Dispatch Center Project Ratification Proclamation No. 991/2016 ""Done at Addis Ababa this 27th 2016 "is hereby corrected and shall be read as "Done at Addis Ababa this 27th day of January 2017."